| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ስያሳ ። |
| ርእስ ፤ | "ከኀይል ፡ ሚዛን ፡ ወደርትዕ ፡ ሚዛን ፨ " |
| ደራሲ ፤ | ወሌ ፡ ነጋ ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2015 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2015-001 |
| ማስታወሻ ፤ | (የግል ፡ አስተያየት ። ) |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ስያሳ

politics | politique | سِيَاسَة

## ከኀይል ፡ ሚዛን ፡ ወደርትዕ ፡ ሚዛን ፨

ወሌ ፡ ነጋ ።

ከታሪኩ ፡ የሚማር ፡ አስተዋይ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ራሱንም ፡ የገዛ ፡ ነው ። በክፉ ፡ ምኞቱ ፡ ከመነዳት ፣ የግፍ ፡ በትርም ፡ ከመኾን ፡ ራሱን ፡ ጠብቆ ፥ ስሕተቱን ፡ አይደግምም ፥ ከጥፋትም ፡ ይድናል ። ራሱን ፡ መግዛት ፡ ተስኖት ፥ የክፉ ፡ ምኞቱ ፡ ባሪያ ፥ አለዚያም ፡ የግፈኞች ፡ መሣሪያ ፡ የኾነው ፡ ኹሉ ፡ ግን ፥ ለጥፋት ፡ ተበጅቷልና ፥ በደመ ፡ ነፍስ ፡ ከመነዳት ፣ ላዘዙትና ፡ እንዳዘዙት ፡ ከመዋል ፡ ሌላ ፡ ማማረጫ ፡ አይኖረውም ፤ ጥፋት ፡ ደጋግሞ ፡ ይጐበኘዋል ።

ኹሉም ፡ ወገን ፡ ርትዕን ፡ አክባሪ ፡ ኾኖ ፡ መኖር ፡ ሲችል ፥ በሰዎች ፡ መኻከልም ፡ ኾነ ፡ በመንግሥታት ፡ መኻከል ፡ ሰላም ፡ ይሰፍናል ። አፍራሻውን ፥ አንዱ ፡ የሌላውን ፡ ንብረት ፡ በመመኘት ፡ ለመንጠቅ ፡ ሲነሣ ፥ ጥል ፡ ይመሠረታል ። ጦርነት ፡ መልኩን ፡ ይለዋውጥ ፡ እንጂ ፥ መነሻው ፥ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፥ የርትዕ ፡ አለመከበርና ፡ የመብት ፡ መጣስ ፡ መኾኑን ፡ የዓለም ፡ ሥልጣኔዎች ፡ ኹሉ ፡ ይስማሙበታል ።

የኮቪድ ፡ ወረርሽኝ ፡ አስደንግጦን ፡ ከራርመን ፥ ከድንጋጤያችን ፡ ገና ፡ ሳንወጣ ፥ አኹን ፡ ደግሞ ፥ የሦስተኛ ፡ ዓለም ፡ ጦርነት ፡ ጕርምርምታው ፡ ተሰማ ። እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የደም ፡ መፋሰስ ፡ መነሻ ፡ ምክንያት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ ስላየለ ፥ ሰላም ፡ ሊደፈርስ ፡ ግዴታ ፡ ኾኖ ፥ ባኹኑ ፡ ሰዓት ፡ አንድም ፡ የዓለም ፡ አካባቢ ፡ በሰላም ፡ ውሎ ፡ በሰላም ፡ የሚያድር ፡ አይገኝም ፤ ወይ ፡ የሽብር ፡ ጥቃት ፣ ወይ ፡ የጅምላ ፡ ግድያ ፣ ወይ ፡ የድንበር ፡ ጦርነት ፣ ወይ ፡ ሰው-ሠራሽ ፡ አደጋ ፣ ወይ ፡ የመንግሥት ፡ ግልበጣ ፡ ... ፡ የዕለት ፡ ተለት ፡ አውራ ፡ ዜናችን ፡ ኾኗል ። ያኹኑ ፡ ግን ፡ የተለየ ፡ ነው ፤ መላ ፡ ዓለም ፡ (በነገሩ ፡ የሌለበትም ፡ ሳይቀርለት) ፡ በቅጽበት ፡ የሚጠፋበት ፡ የ"ንዩክሊየር" ፡ አደጋ ፡ ዐብሮ ፡ መጥቷል ። ባለጊዜዎቹም ፡ ምዕራባውያን ፡ የማይንቁትን ፡ ባለጋራቸውን ፡ አግኝተዋል ።

የ"ንዩክሊየር ፡ ቦምብ" ፡ በሂሮሺማ ፡ እና ፡ በናጋዛኪ ፡ ጕልበቱንና ፡ ክፋቱን ፡ ካሳየበት ፡ ከኹለተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ መደምደሚያ ፡ ወዲህ ፡ በ"ንዩክሊየር" ፡ ኀይል ፡ ሚዛን ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፡ "ሰነፍ ፡ ዕርቅ" ፡ ላለፉት ፡ 77 ፡ ዓመታት ፡ በዓለማችን ፡ ሰፍኖ ፡ ቈይቷል ። በሌላ ፡ አነጋገር ፥ የባሰውን ፡ በመፍራት ፥ ባለጋራዎች ፥ ቀዩን ፡ መሥመር ፡ አክብረው ፥ ከርሱ ፡ በመለስ ፥ የሚጐነታተሉበት ፥ ሲብስባቸውም ፡ በቀዝቃዛ ፡ ጦርነት ፡ ተፋጥጠው ፡ የሚከርሙበት ፡ ወቅት ፡ ነበር ።

ዘንድሮ ፥ ዐዲስ ፡ ነገር ፡ ተፈጥሯል ፤ የሩስያ ፡ እና ፡ የኡክራይና ፡ ጦርነት ፥ ወይም ፡ በመስኮቦች ፡ አባባል ፥ "የሩስያ ፡ እና ፡ የአንግሎ-ሳክሰን ፡ ዕባራ [1] ፡ ጦርነት" ፡ ተዠምሯል ፤ ቀዩ ፡ መሥመር ፡ ተረምዷል ። ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ ከ"ንዩክሊየር" ፡ መሣሪያ ፡ ሌላ ፥ የጅምላ ፡ ፍጅት ፡ መሣሪያዎች ፡ ታጣቂዎች ፡ ናቸው ። ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ ተደራቢዎች ፡ መንግሥታት ፡ አሏቸው ። አንደኛው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፥ የባሰው ፡ ቢመጣ ፥ በ"ንዩክሊየር"ም ፡ ኾነ ፡ በሌላ ፡ የጅምላ ፡ ፍጅት ፡ መሣሪያ ፡ ከማጥቃት / ከመከላከል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንደማይል ፡ ደጋግሞ ፡ አስታውቋል ። ለዚህም ፡ ጭካኔው ፥ የባለጋራዎቹ ፡ በህልውናው ፡ መምጣት ፡ ምክንያቱ ፡ መኾኑን ፡ ነግሯል ። ባለጋራዎቹ ፡ ደግሞ ፥ የቀረበባቸውን ፡ ውንጀላ ፡ ለማስተባበል ፡ ሳይገደዱ ፥ እነሱም ፡ ያንኑ ፡ ያኽል ፡ በመጨከን ፡— « ምን ፡ እንዳትኾን ! » ፡ የሚሉት ፡ መስለዋል ፤ ለተጠቃችውም ፡ ወገን ፥ ለኡክራይና ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ድጋፍ ፡ አግበስብሰው ፡ አቅርበውላት ፥ ጦርነቱን ፡ አፋፍመውታል ። ነገሩ ፡ ተካሯል ፤ ሰላማዊ ፡ መፍትሔም ፡ ያጣ ፡ ይመስላል ።

የዶክተር ፡ ኪሲንገ(ጀ)ር ፡ "የኀይል ፡ ሚዛን ፡ መርሕ" ፡ አፍጅቶና ፡ መክኖ ፥ እዚህ ፡ ላይ ፡ አገልግሎቱ ፡ በይፉ ፡ አብቅቷል ። ጠቡ ፡ ለገላጋይ ፡ አስቸግሮ ፥ ዓለም ፡ ወደመጠፋፋት ፡ ዘግናኝ ፡ ዐዘቅት ፡ ስትንሸራተት ፥ እንሆ ፡ ዐቅመ ፡ ቢሶች ፡ ኾነን ፡ ፈዝዘን ፡ እናያታለን ።

መፍትሔው ፡ ከኀያላኑ ፡ ወገን ፡ እንደማይገኝ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ማስረጃ ፡ የለም ። የኹላችን ፡ ህልውና ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ወደቀብን ፥ ለደኅንነታችን ፡ ስንል ፥ በእየበኩላችን ፡ የመፍትሔ ፡ ሐሳብን ፡ ለማፍለቅ ፡ እንገደዳለን ። ጕዳዩ ፡ ኹላችንን ፡ ይመለከታል ፤ ባንወድም ፡ በግድ ፡ ያገባናል ። ችግሩ ፡ ከተራራም ፡ በላይ ፡

1 አንግሎ-ሳክሰን ፡ ዕባራ ፤ Anglo-Saxon coalition ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

ዓለምን ፡ ያከላልና ፥ መፍትሔውን ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡ የምንደረስበት ፡ አይመስለኝም ። የመፍትሔ ፡ ሐሳብን ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ሊያፈልቅ ፡ ይችላልና ፥ የመሰለኝን ፡ የመፍትሔ ፡ ሐሳብ ፡ እንደሚከተለው ፡ ላንባብያን ፡ አቅርቤያለኹ ።

በደል ፡ ካለ ፥ በዳይና ፡ ተበዳይም ፡ አለ ፤ በመዠመሪያ ፥ ተበድያለኹ ፡ የሚለው ፡ ወገን ፡ በደሉን ፡ በዓለም ፡ አደባባይ ፡ የሚያስሰማበት ፡ አገባብ ፡ ሊሰጅለት ፡ ይገባል ። ይህ ፥ በቀዳሚነት ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ኀላፊነትና ፡ ሥራ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ራሱ ፥ የሚንቀሳቀሰው ፡ በኀያላን ፡ አባላት ፡ መንግሥታቱ ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ከነዚህ ፡ መንግሥታት ፡ ጥቂት ፡ የማይባሉት ፥ ለወከላቸው ፡ ሕዝብ ፡ ፈቃድ ፡ ከመገዛትና ፡ ከመታመን ፡ ይልቅ ፡ በሌላ ፡ ስውር ፡ ኀይል ፡ የሚዘወሩ ፡ እስኪመስል ፡ ድረስ ፥ የሕዝባቸውን ፡ ስሜት ፡ ከቍጥር ፡ አይጥፉትም ፤ ሲያስፈልጋቸውም ፡ በማዘናጊያ ፡ ይደልሉታል ፡ ወይ ፡ ይሸነግሉታል ። ለዚህም ፡ እውነት ፡ ጥቂት ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ፦

- አንደኛው ፡ ምክንያት ፥ እያንዳንዱ ፡ የዓለም ፡ መንግሥት ፥ የእየራሱን ፡ ሕዝብ ፡ ኹለንተናዊ ፡ ደኅንነት ፡ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ ለመጠበቅ ፡ ይጥራል ፤ ኾኖም ፥ አንዳንድ ፡ መንግሥታት ፡ የውጭ ፡ ተጽዕኖ ፡ ስለሚጠናባቸው ፥ በተለይ ፡ ስለውጭ ፡ ስያስ ፡ (ወይም ፡ ስለ ፡ "foreign policy") ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ጥያቄ ፡ ከሕዝባቸው ፡ እንዳይነሣባቸው ፥ የሕዝባቸውን ፡ ትኵረት ፡ የመቀየስ ፣ ቍጣውን ፡ የማብረድና ፡ የማባበል ፣ ከሥጋቱ ፡ የማዘናጋት ፡ ዘዴዎች ፡ አሏቸው ። በዚህ ፡ ምክንያት ፥ የውጭ ፡ ስያሳቸውን ፡ በጣፋጭ ፡ ቃላት ፡ ዐጅለው ፥ ውስጡን ፡ ግን ፡ በግፍ ፡ ተባባሪነት ፡ አለዚያም ፡ በዐድር-ባይነት ፡ ይቀርጹትና ፥ የአህጉራውያን ፡ ድርጅቶችን ፡ ሥምረትና ፡ ደንብ ፡ ማክበርም ፡ ኾነ ፡ ሀገራዊ ፡ መብታቸውን ፡ ማስከበር ፡ ይሳናቸዋል ።
- ኹለተኛው ፡ ምክንያት ፥ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ስያሳዊ ፡ ችግር ፡ ሲገጥማቸው ፥ አንዳንድ ፡ መንግሥታት ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ ሕጸጽ ፡ ያለባቸው ፡ መንግሥታት ፥ የውጭ ፡ ጠላትን ፡ ፈጥሮ ፡ ሕዝብን ፡ ማወናበዳቸው ፡ የተለመደ ፡ ኾኗል ።
- ሦስተኛው ፡ ምክንያት ፥ በምልከኝነት ፡ (ወይም ፥ በ imperialist-እነት) ፡ የታወቁ ፡ የዘመኑ ፡ ኀያላን ፡ መንግሥታት ፥ በ"democracy" ፡ የ"አንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ድምፅ" ፡ መርሕ ፡ በሕዝብ ፡ የተመረጡ ፡ አስተዳደሮችን ፡ እያፈራረቁ ፡ ሕዝባቸውን ፡ ቢደልሉም ፡ ቅሉ ፥ የውጭ ፡ ስያሳቸው ፥ በቅድመ-"democracy" ፡ ዘመን ፡ የውስጥ ፡ ሥርዐታቸው ፡ የነበረውን ፡ "feudalism" ፡ አገልብቶ ፡ በጽሚት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ በመዘርጋት ፥ በገባሮች ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ የሚያውሉት ፡ ግፈኛ ፡ ስልታቸው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ፍትሕ ፡ እና ፡ ርትዕን ፡ በዓለም ፡ ደረጃ ፡ ሲረመርሟቸው ፡ ይኖራሉ ።

በውጭ ፡ ስያስ ፡ ረገድ ፥ ይህ ፡ የመንግሥታት ፡ አሠራር ፡ እሕዝብ ፡ ቍጥጥር ፡ ተመልሶ ፡ እስካልገባ ፡ ድረስ ፥ የምልክዮሽ ፡ (ወይም ፡ የ imperialism) ፡ ጦስ ፡ የዓለምን ፡ ሰላም ፡ ሲያናጋውና ፥ በዘመን ፡ ብዛትም ፡ መላ ፡ ዓለምን ፡ ወደ ፡ ፍጹም ፡ ጥፋት ፡ ሲገፈትረው ፡ ይኖራል ።

"እሳት ፡ ለፈጀው ፡ ምን ፡ ይብጀው ፡፡ " የጦርነት ፡ መልካም ፡ የለውምና ፥ በኡክራይናም ፡ ኾነ ፡ በሌሎች ፡ ሀገሮች ፥ የኀያላኑ ፡ ዐምባ ፡ ጓሮ ፡ በሰላማውያን ፡ ነዋሪዎች ፡ የሚዘገንን ፡ መከራን ፡ ያስከትላል ። ግፉ ፡ ሲበዛም ፥ አይተውና ፡ ሰምተው ፡ ዝም ፡ ወደእሚሉት ፡ መዛመቱ ፡ አይቀርም ፤ አይተንና ፡ ሰምተን ፡ ዝም ፡ አንበል ።

መንግሥታት ፥ ኀያላን ፡ ቢባሉም ፡ ባይባሉም ፥ ኹሉም ፡ በሥልጡንሕዝባዊ ፡ (በ democratic) ፡ መንገድ ፡ ለሕዝባቸው ፡ ተጠሪዎች ፡ ሊኾኑ ፡ ይገባል ፤ **የእያንዳንዱ ፡ መንግሥት ፡ ሕዝብ ፡ የመንግሥቱን ፡ የውጭ ፡ ስያስ ፡ የሚያጠይቅበትን ፡ የምርመራና ፡ የቍጥጥር ፡ ሥርዐት ፡ ሊያበጅ ፡ ይገባል** ። ለዚህ ፡ የመዠመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ወንጠፍት ፡ ድርብ ፡ የሚኾን ፡ የኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ ወንጠፍት ፡ ደግሞ ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታትና ፡ በአህጉራውያን ፡ ድርጅቶች ፡ ደረጃ ፡ መበጀት ፡ ይኖርበታል ።

ሥልጡንሕዝባውያን ፡ በተባሉት ፡ ሀገሮች ፥ ቀጣዩን ፡ አስተዳደር ፡ ለመሠየም ፡ በሚደረግ ፡ ምርጫ ፡ ኹሉ ፥ ተወዳዳሪዎች ፡ ቡድኖች ፥ ስለዋጋ ፡ ንረት ፣ ስለሥራ ፡ ዕድል ፡ መፍጠር ፣ ስለ ፡ ትምህርት ፣ ስለ ፡ ዕርሻ ፣ ስለ ፡ ጤና ፣ ወዘተርፈ ፡ ... ፡ ስያሶቻቸውን ፡ ለሕዝብ ፡ በሚያስተዋውቁበት ፡ ሰዓት ፥ በውጭ ፡ ስያስ ፡ ረገድ ፦

- ሰላምን ፡ ለማስፈን ፡ ምን ፡ ዕቅድ ፡ እንዳላቸው ፡ የሚጠየቁበት ፤
- የቀደመውም ፡ አስተዳደር ፡ ሰላምን ፡ በማስፈን ፡ ረገድ ፡ ያስገኘው ፡ ውጤት ፡ የሚገመገምበት ፤
- የሀገሪቱ ፡ የውጭ ፡ ስያስ ፡ አህጉራዊ ፡ ግንኙነትን ፡ (international relations ን) ፡ በመንፈሱም ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።

በቃሉም ፡ ያከበረና ፥ ባፈጻጸምም ፡ ረገድ ፥ ለውጭ ፡ ተጽዕኖ ፡ የማይበገር ፡ መኾኑ ፡ የሚረጋገጥበት ፤

ዐዲስ ፡ የምርመራ ፣ የፍተሻ ፣ የግደባ ፡ ሥርዐት ፡ ሊበጅና ፡ ሊለመድ ፡ ይገባል ። ያንድ ፡ ሀገር ፡ የውጭ ፡ ስያስ ፥ ከጥርየታዊ ፡ ስያስና ፡ ከማኅበራዊ ፡ ስያስ ፡ ያላነሰ ፥ ምናልባትም ፡ የባሰ ፡ መዘዝ ፡ ሊኖረው ፡ ስለሚችል ፥ በምርጫ ፡ ዘመቻ ፡ ወቅት ፥ የውጭ ፡ ስያስ ፡ ከዋነኛዎቹ ፡ የመመረጫ ፡ አርእስት ፡ አንዱ ፡ ርእስ ፡ ኾኖ ፡ እንዲቀርብ ፡ ሰፊ ፡ የቅስቀሳና ፡ የማስገንዘቢያ ፡ ዘመቻ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ መስፋፋት ፡ ይኖርበታል ።

ባጠቃላይ ፡ የዓለም ፡ ሰላም ፡ ለዘለቄታው ፡ እንዲረጋገጥ ፥ አህጉራዊው ፡ ግንኙነት ፦

- የእያንዳንዱን ፡ ሀገር ፡ እግዚእና ፡ እና ፡ ሐራነት ፡ በሚያስከብር ፡ ሕጋዊ ፡ ምሕቃፍ ፡ ውስጥ ፡ መካኼድ ፤
- ባስሠራር ፡ ግልጽነት ፡ መከናወን ፤
- ጥሰት ፡ ሲፈጸም ፡ ደግሞ ፥ ወዲያው ፡ ጥሰቱን ፡ የሚያግድና ፡ የሚያድብ ፥ ዕርማቱንም ፡ የሚያስገድድ ፡ የተቋም ፡ ተሐድሶ ፡ በእየረድፉ ፡ መፈጸም ፡ ይኖርበታል ።

የመዠመሪያው ፡ ረድፍ ፥ በእያንዳንዱ ፡ ሀገር ፥ እስከሕገ ፡ መንግሥት ፡ ማሻሻል ፡ የሚኼድ ፡ የደንብና ፡ የሥርዐት ፡ ማሻሻያን ፡ ይጠይቃል ።

ኹለተኛው ፡ ረድፍ ፥ ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ሥምረት ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አህጉራውያን ፡ ድርጅቶች ፡ ደንብ ፡ ድረስ ፥ በመንግሥታት ፡ መኻከል ፡ የሚኖርን ፡ ስውርም ፡ ኾነ ፡ ይፋ ፡ ተጽዕኖ ፡ በግልጽ ፡ የሚያስወግድና ፥ በእኩልነትና ፡ በመከባበር ፡ ላይ ፡ የተመሠረተ ፥ **በርትዕ ፡ ሚዛን** ፡ ላይ ፡ የቆመ ፡ የመንግሥታት ፡ ሱታፌን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ጥብቅ ፡ እና ፡ ግልጽ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲኖር ፡ ማስቻል ፡ ይኾናል ።

እመግቢያው ፡ ላይ ፡ እንደተገለጸው ፥ የጦርነት ፡ ኹሉ ፡ መነሻው ፥ አንዱ ፡ ወገን ፡ የማይገባውን ፡ የሌላውን ፡ ወገን ፡ ንብረት ፡ በመመኘት ፥ በጕልበትም ፡ ኾነ ፡ በተንኰልና ፡ በሸር ፡ ሲነጥቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ከንግዲህ ፡ አህጉራዊው ፡ ሥርዐት ፡ ይህን ፡ አደራረግ ፡ የሚከለክልበትን ፡ ሕጋዊ ፡ ምሕቃፍ ፡ ለማብጀትና ፡ ለማጠናከር ፡ መንቀሳቀስ ፡ ይኖርበታል ። ይህን ፡ ማሻሻያ ፡ የሚቃወሙና ፡ የሚያሰናክሉ ፡ ምልከኞች ፡ ኀይሎች ፡ ቢኖሩም ፡ እንኳ ፥ አጠቃላይ ፡ ጥፋት ፡ ያንዣበበበት ፡ የዓለም ፡ ሕዝብ ፡ በእየሀገሩ ፡ ውስጥ ፡ ጽዳቱን ፡ ራሱ ፡ ካካኼደ ፥ "ጨለማን ፡ ተገን ፡ አድርገው" ፡ ዓለምን ፡ የሚበዘብዙትን ፡ ጥቂቶች ፡ ፈያታውያን ፡ አደብ ፡ በማስገዛት ፥ የራሱንም ፡ የዓለምንም ፡ ህልውና ፡ ማስጠበቅ ፡ ይቻለዋል ።

ዋናው ፡ ጥያቄ ፦ *« ይህ ፡ ማሻሻያ ፡ የሚደረግበት ፡ ሰዓት ፡ አኹን ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ግድ ፡ በጦርነት ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ተለብልቦ ፡ ዐልፎ ፥ ከጦርነቱ ፡ የተረፉት ፡ ዕድለኞች ፡ ከመከራቸው ፡ ተምረው ፡ ዐዲሱን ፡ "የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ሥምረት" ፡ ሲያጸድቁ ፡ ይኾን ፧ »* ፡ የሚለው ፡ ጥያቄ ፡ ይመስለኛል ። ጦርነቱ ፡ ዓለምን ፡ እንደ ፡ ወረርሽኝ ፡ ለኰፍ ፡ አድርጓት ፡ የሚያልፍ ፡ መኾኑን ፡ የዓለም ፡ ኅብረተሰብ ፡ ቢያረጋግጥ ፥ ምናልባት ፡ ሥራውን ፡ ቢያዘገየውም ፥ የሚከፈለው ፡ ዋጋ ፡ ብዙ ፡ አያሳስብ ፡ ይኾናል ፤ የሚልዮን ፡ የኹለት ፡ ሚልዮን ፡ ሕዝብ ፡ ዕልቂት ፡ ተለምዷል ፡ ... ። ሦስተኛው ፡ የዓለም ፡ ጦርነት ፡ ግን ፡ እኹላችን ፡ ላይ ፡ ይግባኝ ፡ የሌለው ፡ የ"ይሞት ፡ በቃ" ፡ ብይን ፡ ስለሚኾን ፥ ጕዳዩ ፡ ጊዜ ፡ የማይሰጠው ፡ አጣዳፊ ፡ ነውና ፥ ለጥያቄው ፡ መልሱ ፡ ግልጽ ፡ ይመስለኛል ፠


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2015 ፡ ዓ.ም. ።